

## ኒቆዲሞስ

- ኒቆዲሞስ የፈሪሳውያን አለቃ ነበር።
  ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረጋቸውን ተአምራት ተመልክቷል፤ ስለእርሱም ብዙ ሰምቷል። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከ እውነተኛ መምህር እንደሆነም ያምን ነበር። ኢየሱስን ሊያገኘውና ከእርሱ ጋራ ሊነጋገር ይፈልግ ነበር። ሆኖም እስኪመሽ ድረስ ይጠብቅ ነበር።

- ኒቆዲሞስ ኢየሱስን ካገኘው በኋላ እንዲህ አለው "በእውነት አንድ ሰው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በስተቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት ሊያደርግ አይቸልም።" አለው።. ከዚህ በኋላም ኢየሱስ ኒቆዲሞስን ማስተማር ጀመረ። አንድ ሰው መንግስተ ሰማያትን ማየት የሚሻ ከሆነ እንደገና መወለድ እንደሚኖርበት ነገረው።
  "እንደገና መወለድ!" ኒቆዲሞስ ተደነቀ። ኒቆዲሞስ ራሱን እንደገና እንደ ሕፃን ልጅ አድርጎ በአእምሮው ሳለ። "እንዴት ሊሆን ይችላል?" እንዴት ትልቅ ሰው እንደገና ሕፃን ሊሆንና እንደገና ሊወለድ ይቻለዋል?" ብሎ እጅግ ተገረመ።

- ኢየሱስ ግን ሲናገር የነበረው በአካል እንደገና ሰለመወለድ አልነበረም።. ስለመንፈሳዊ መወለድ ነበር ኢየሱስ ያወራው። አንድ ሰው ከመንፈስና ከውኃ መወለድ ያስፈልገዋል ብሎ ኢየሱስ ተናገረ። ንፋስ ሲነፍስ እንደማይታይ በመንፈስ መወለድም የሚታይ ነገር እንዳልሆነ ለኒቆዲሞስ ገለፀለት። በመንፈስ የተወለደ ሰው በአይን ሲመለከቱት ምንም የተለወጠ ላይመስል ይችላል። ሆኖም በውስጥ የተለወጠ ሰው ነው።

❈ በምድረ በዳ እባቦች እስራኤላውያንን ሲገድሉ እግዚአብሔር ሙሴን የነሐስ እባብ ሰርቶ በእንጨት ላይ እንዲሰቅለውና እርሱን የተመለከተው ከእባቡ መርዝ እንደሚድን ገለፀ። ኢየሱስም እንዲሁ ሊሰቀልና በእርሱ የሚያምን ሁሉ እንደሚድን የዘላለም ሕይወትንም እንደሚያገኝ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ገለፀለት።

❈ ከዚያም ኢየሱስ እነኝህን ደስ የሚሉ ቃላት ተናገረ። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"

❈ ኢየሱስ በሰዎች ላይ ለመፍረድ ሳይሆን ሰዎችን ለማዳን እንደመጣ ተናገረ።

❈ ስለኒቆዲሞስ እንደገና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናነበው ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኋላ ነው። የአርማትያሱ ዮሴፍ ባለጠጋ ሰው ሲሆን የአይሁድ ሸንጎ አባልም ነበር።. መልካም ሰው ከመሆኑም በሻገር የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይም ነበር። የእግዚአብሔርን መንግስት መገለጥ የሚጠባበቅ ሰው ነበር። እንዲሁም ኢየሱስ ለዓለም እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ እንደሆነም ያምን ነበር። በድፍረት ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን አስከሬን እንዲሰጠው ጠየቀ። ከዚህ ሰው ጋር አብሮ የኢየሱስን አስከሬን ለመውሰድ የመጣው ሌላኛው ሰው ኒቆዲሞስ ነበር።

❈ በአይሁድ ልማድ መሠረት የሟችን አስከሬን በተለያዩ ቅመማ ቅመማት በማሸት ለቀብሩ ማዘጋጀት የተለመደ ነበር። ስለዚህ የተለያዩ ቅመማ ቅመም ገዙ። ከዚያም የኢየሱስን አስከሬን ለቀብር አዘጋጁ። ከዚያም በከፈን ሸፈኑት።

❈ ኢየሱስ በተሰቀለበት አካባቢ አንድ የአትክልት ስፍራ ነበር። ዮሴፍም በዚህ አካባቢ የገዛው መቃብር ነበር። ይህም መቃብር ከዚህ በፊት ማንም አልተቀበረበትም። ይህ የመቃብር ስፍራ ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተጠርቦ የተሰራ መቃብር ነበር። የኢየሱስን አስከሬን በዚህ መቃብር ውስጥ ካስቀመጡት በኋላ የመቃብሩን ደጅ ትልቅ ድንጋይ አንከባለው ዘጉት። መቅደላዊት ማርያምና ሌላዋ ማርያም ከመቃብሩ ፊት ለፊት ተቀምጠው ነበር።

*የኒቆዲሞስ ታሪክ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 3፡1 – 21 ውስጥ ይገኛል።*

http://gardenofpraise.com